**የኢትዮጵያ**
**ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)**
**ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL (EHRCO)**

**አስቸኳይ ጋዜጣዊ መግለጫ**

# መንግስት እየተፈጸሙ ላሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በቂ ትኩረት ይስጥ!

መጋቢት 13/2015 ዓ.ም

## በአማራ ክልል ውስጥ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፡

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምስራቅ ጎጃም ዞን ደብረ ኤልያስ ወረዳ በብሔረ ብፁዓን አጼ መልካ ስላሴ ገዳም የዞኑና የወረዳው አስተዳደር ለገዳሙና ለምዕመናኑ የተለያዩ ስሞችን በመስጠትና አላግባብ በመፈረጅ ሽፍታ ይደብቃል፣ የተቃዋሚ ፓርቲ ነው፣ ለህገ-ወጥ ግለሰቦች ከለላ ይሰጣል በሚል የዞኑና የወረዳው አስተዳደር በቅንጅት በገዳሙ እና በምዕመኑ ላይ ጥር 22 ቀን 2015 ዓ.ም በመንግስት የጸጥታ ሃይሎች በተፈጸመ ጥቃት 10 ወንድ እና 1 ሴት በድምሩ 11 ጸበልተኞችና መናኞች እንደተገደሉ፣ 9 ሴት እና 8 ወንድ በድምሩ 17 መናኞችና ጸበልተኞች ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት እንደደረሰባቸውና ምንም አይነት የህክምና አገልግሎትም እንዳላገኙ ኢሰመጉ ከሟችና ከተጎጂ ቤተሰቦች መረጃ ያገኘ ሲሆን ይህንንም መረጃ ተከትሎ ኢሰመጉ የምርመራ ስራ ለመስራት መጋቢት 1 ቀን 2015 ዓ.ም የሰብዓዊ መብቶች የመርማሪ ባለሙያ ወደቦታው ቢልክም በወረዳው አባ ገኔ ቤት ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ላይ ባሉ ኬላ በሚጠብቁ የመንግስት የጸጥታ አካላት ክልከላ ተደርጎበታል፡፡

## በሲዳማ ክልልና በኦሮሚያ ክልል አዋሳኝ ላይ በተፈጠረ ግጭት የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፡

በሲዳማ ክልል ጭሪ ወረዳ ላይ ለስብሰባ በተጠሩ የሲዳማ ተወላጆች ላይ በታጣቂዎች በተፈጸመ ጥቃት 12 ሰላማዊ የአካባቢው ነዋሪዎች የተገደሉ ሲሆን ይህንንም ተከትሎ በአካባቢው ግጭቱ ቀጥሎ በርካታ ንጹሀን ሰዎች ከሁለቱም ክልሎች እንደሞቱና ጉዳዩ የብሔር ግጭት መልክን ይዞ መቀጠሉን በእዚህም ምክንያት የሰዎች ህይወት ማለፉን፣ የአካል ጉዳት መድረሱን፣ ንብረት መውደሙን እና በርካታ ሰዎች መፈናቀላቸውን ኢሰመጉ ከአካባቢው ነዋሪዎች ባገኘው መረጃ ለመረዳት ችሏል፡፡

## በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፡

በምስራቅ ወለጋ ዞን ሳሲጋ ወረዳ በ19/06/2015 ዓ.ም ከሀሮ ፈይሳ ቀበሌ በወረዳው ፖሊስ ጣቢያ ታስረው የሚገኙ ጓደኞቻቸውን ለመጠየቅ የሄዱ ሁለት ወጣቶ ችን የአካባቢው የመንግስት የጸጥታ አካላት ከቤተሰቦቻቸው ለይተው በመያዝ ካቆዩ በኋላ ወደ ጫካ በመወሰድ ሌላ ከብት የሚጠብቅ አንድ ወጣትን አብሮ በመጨመር ሶስቱንም ከህግ አግባብ ውጪ እንደገደሏቸውና አስከሬናቸውም በ20/06/2015 ዓ.ም ተገኝቶ በ21/06/2015 ዓ.ም የቀብር ስነስርዓታቸው በሀሮ ፌይሳ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን እንደተፈጸመ ኢሰመጉ ከአካባቢው ነዋሪዎች ባገኘው መረጃ ለመረዳት ችሏል፡፡

በተጨማሪም በጉጂ፣ ቦረናና ባሌ አካባቢዎች ከአስተዳደር ወሰን ጋር በተያያዘ በጉጂ ዞን በተለያዩ አካባቢዎች የተቃውሞ ሰልፎች የተደረጉ ሲሆን በቦሬ ከተማ በተደረገው ሰልፍ 4 ወጣቶች ከአካባቢው የመንግስት የጸጥታ አካላት በተተኮሰ ጥይት ህይወታቸው ማለፉን ኢሰመጉ ከአካባቢ ነዋሪዎች ባገኘው መረጃ ለመረዳት ችሏል፡፡

በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ዳኖ ወረዳ በዳኢሉ ቀበሌ በ24/06/2015 ዓ.ም የአንድ ቤተሰብ አባል የሆኑት አቶ ዘውዴ ከበደ፣ አቶ ሀብታሙ ከበደ፣ አቶ ዳምጠው ከበደና ሙሉ ዘውዴ እህል እየወቁ ባሉበት ውድማ በ ታጣቂዎች ግድያ እንደተፈጸመባቸው ኢሰመጉ ከአካባቢው ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡

## በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ውስጥ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች

በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ሀላባ ዞን ሀላባ ቁሊቶ ከተማ በሚገኘው ሀላባ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ የሆነችው የ14 ዓመት ታዳጊ ሊዲያ አበራ በትምህርት ቤት ቅጥር ጊቢ በጓደኞቿ ላይ ድግምት ሰርታለች በሚል በ22/06/2015 ዓ.ም በፖሊስ ተይዛ ለአምስት ቀን ያህል ከቆየች በኋላ ሀላባ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀርባ በተጠየቀባት የ14 ቀን የጊዜ ቀጠሮ መሰረት ወደ ሀላባ ቁሊቶ ማረሚያ ቤት ተወስዳለች፡፡ በተማሪ ሊዲያ አበራ ላይ ማስፈራራትና ዛቻ ሲደርስ እንደነበር እንዲሁም በምርመራ ወቅት ልብሷን በማስወለቅ ፍተሻ እንደተደረገባት ተረድተናል፡፡ ይህንንም ተከትሎ በ06/07/2015 ዓ.ም የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ሰልፍ እንደወጡ በመቀጠልም 08/07/2015 ዓ.ም ፍርድ ቤቱ በ30,000 (ሰላሳ ሺ) ብር ዋስ እንድትፈታ በመወሰኑ ከእስር መለቀቋን ኢሰመጉ ከአካባቢው ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡

በጋሙ ባባ ወረዳ ኩይሌ ቀበሌ ለወረዳ አስተዳደር አቤቱታ ለምን አቀረባችሁና ለኢሰመጉ መረጃ ለምን ትሰጣላችሁ በሚል መክንያት ሁለት የኢሰመጉ አባላትና ሁለት ሌሎች ሰዎች በአጠቃላይ አራት ሰዎች በአካባቢው ፖሊስ የታሰሩ ሲሆን እነዚህ አራት ሰዎች ይህ መግለጫ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ ቃል አለመስጠታቸውንና ፍርድ ቤት አለመቅረባቸውን፣ በአማሮ ልዩ ወረዳ ያሉ ተፈናቃዮች ከኮሬ ብሔረሰብ አባል ውጪ የሆኑት በቡነቲ ወረዳ መኖር መከልከላቸውን፣ ምንም አይነት ሰብዓዊ ድጋፍ እና እርዳታ እንደማይደረግላቸው፣ አንዳንድ ከኮሬ ብሔረሰብ ውጪ የሆኑ ሰዎችን ከህግ አግባብ ውጪ በማሰር ንብረታቸው ጭምር እንደሚወረስባቸው፣ በጋሙ ባባ ወረዳ የጤና መድህን አባል ለምን አልሆናችሁም በሚል ሰባት ሰዎች ታስረው እንደነበርና ኢሰመጉ ከቀበሌው ሊቀመንበር ጋር ባደረገው ውይይት የተፈቱ ሲሆን ነገርግን የቀበሌውን ሊቀመንበር ለ ምን የታሰሩትን ፈታህ እና መረጃ ለምን ለኢሰመጉ ሰጠህ በሚል በወረዳው አመራር ውስጥ ያለ ግለሰብ በህዝብ የተመረጠውን የቀበሌውን ሊቀመንበር ከሀላፊነት በማንሰት ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ በእስር ላይ እንደሚገኝ፣ በደራሼ ልዩ ወረዳ የቀድሞ አመራር ደጋፊና ቤተሰብ ናችሁ በሚል ቤታቸው ለፈረሰባው ሰዎች የወረዳው ካቢኔ በወሰነው መሰረት ለእያንዳንዳቸው የምግብ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን ሌሎች የአካባቢው አመራሮች ከእኛ እውቅና ውጪ ለም ን ድጋፍ ታደርጋላች በሚል ድጋፉን የሰጡ ስም ንት ሰ ዎችን እንዳሰሩና ከ14/06/2015 ዓ.ም ጀምሮ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ የታሰሩት ሰዎች ፍርድ ቤት እንዳልቀረቡ ኢሰመጉ ከአካባቢው ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡

## በአዲስ አበባ እና በኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ አስተዳደር ውስጥ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፡

በአዲስ አበባ እና በኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ አስተዳደር ውስጥ እየተፈጸሙ ያሉ የቤት ፈረሳ እንቅስቃሴዎችን አስመልክቶ በተደጋጋሚ መግለጫ ማውጣቱ የሚታወስ ሲሆን ይህ ድርጊት አሁንም በሁለቱም አካባቢዎች መቀጠሉንና ከድርጊቱም ጋር ተያይዞ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እየተፈጸሙ መሆኑን የሚያሳዩ መረጃዎች ለኢሰመጉ ደርሰውታል፡፡ ከእዚህ ጉዳይ ጋር ተያይዞ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን አስመልክቶ ኢሰመጉ ወደፊት የ ምርመራ ስራዎችን በመስራት ሰፋ ያለ ዘገባን የሚያቀርብ ይሆናል፡፡

በተጨማሪም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሰብዓዊ መብቶች ተቋማት እና በሚዲያ ላይ በተሰማሩ ተቋማት ላይ የቢሮ ሰበራ አና ዝርፊያዎች እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡ ለአዚህም ማሳያነት ዩሪካ ቲቪና ሬዲዮ የድርጅቱ ቢሮ የሚገኝበት ተስኒም ህንጻ አምስተኛ ፎቅ መጋቢት 10 ቀን 2015 ዓ.ም የተለየዩ እቃዎች መዘረፉና በተመሳሳይ ቀን ኢትዮ 251 አራት ኪሎ ድንቅ ስራ ኮምፐሌክስ ላይ የሚገኘው ቢሮ ተሰብሮ የተለያዩ የተቋሙ ንብረቶች መዘረፋቸውን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡

## እየተፈጸሙ ያሉ እገታዎችና ድብደባዎች፡

በአገራችን ኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጋዜጠኞች፣ በፖለቲካ ፓርቲ አባላትና አመራሮች፣ በማህበረሰብ አንቂዎችና በሌሎች ሰዎች ላይ ህገ ወጥ እስሮች፣ እገታዎች፣ ድብደባና ኢሰብዓዊ የሆኑ ድርጊቶች እየተፈጸሙ ይገኛል፡፡ ለእዚህም ማሳያነት በጋዜጠኛ ጎበዜ ሲሳይ ላይ ሚያዚያ 23 ቀን 2014 ዓ.ም የተፈጸመው፣ በአቶ ስንታየሁ ቸኮል ላይ ግንቦት 19 ቀን 2014 ዓ.ም የተፈጸመውና ግንቦት 20 ቀን 2014 ዓ.ም በሰባት የአሻራ ሚዲያ ባለሙያዎች ላይ የተፈጸሙት ድርጊቶች ማሳያ ሲሆኑ **ይህ ድርጊት አሁንም ቀጥሎ** የየኛ ቲቪ ጋዜጠኛ የሆነው አቶ ንጉሴ ብርሀኑ መጋቢት 06 ቀን 2015 ዓ.ም ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች ከመካኒሳ አካባቢ ታፍኖ እንደተወሰደና ከፍተኛ ድብደባ ከተፈጸመበት በኋላ መለቀቁንና በደረሰበት ድብደባ ምክንያት ራሱን በመሳቱ በሆስፒታል ህክምና ሲከታተል መቆየቱን እንዲሁም በተመሳሳይ የታሪክ መምህር፣ ተመራማሪና እና የማህበረሰብ አንቂ የሆነው ታዬ ቦጋለ አረጋ መጋቢት 08 ቀን 2015 ዓ.ም ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ከመኖሪያ ቤቱ አካባቢ በታጣቂ ሰዎች በመኪና ከህግ አግባብ ውጬ ተይዞ ወደ ማያውቀው አካባቢ ተወስዶ ኢ-ሰብዓዊ የሆነ ጭካኔ የተሞላበት ድብደባ፣ ማሰቃየት፣ ዛቻና ማስፈራራት ተፈጽሞበት ከአራት ቀን ቆይታ በኋላ መጋቢት 11 ቀ 2015 ዓ.ም አመሻሽ ላይ ከተያዘበት ቦታ ተለቆ ከቤተሰቦቹ ጋር መቀላቀሉን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል ኢሰመጉ ኢሰመጉ ከላይ የተጠሱትን የአፈና ድርጊቶች አስመልክቶ ጥቃቶቹ ከተፈጸሙበት ጊዜ አንስቶ ጉዳዩን ሲከታተል እንደቆየና ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ ከተጎጂዎቹ ለማግኘት ጥረት ቢደረግም ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ሁኔታዎች አመቺ ባለመሆናቸው ምክንያት ይህ መግለጫ ሊዘገይ እንደቻለ ለመግለጽ ይወዳል፡፡ ይህ ድርጊት እየተደጋገመ በመምጣቱና ድርጊቱን በፈጸሙ አካላት ላይ ምንም አይነት የህግ ተጠያቂነት ባለመመስረቱ ኢሰመጉ ያሳስበዋል ይህ ህገወጥ ድርጊትም እንዲቆም እንዲሁም ድርጊቱን የፈፀሙ አካላትም ተጠያቂ እንዲደረጉ ኢሰመጉ ጥሪ ያቀርባል።

## በፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ የተፈጸሙ ከሰብዓዊ መብቶች ጋር ግንኙነት ያላቸው ጉዳዮች፡

የፖለቲካ ምህዳሩ መሻሻል ካሳዩ ዘርፎች መካከል አንዱ የነበረ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በፖሊቲካ ፓርቲዎች፣ በአመራሮቻቸው ላይ እና በአባላቶችቸው ላይ የሚፈጸሙ ድርጊቶች ከሰብዓዊ መብቶች አሳቤዎች በተቃርኖ የሚቆሙ፣ የሰዎችን የሰብዓዊ መብቶች የሚጥሱ፣ የፖለቲካ ምህዳሩን የሚያጠቡ፣ በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታው ላይ አደጋን የሚጥሉ እና ፖለቲካ ፓርቲዎችን በማዳከም ሰዎች በአገራቸው መንግስት ውስጥ በቀጥታ ወይም በነጻ በመረጧቸው ወኪሎቻቸው አማካኝነት እንዳይሳተፉ የሚያደርጉ ድርጊቶች ሲሆኑ በቅርቡ መጋቢት 02 ቀን 2015 ዓ.ም የባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ እና እናት ፓርቲ የካቲት 26 ቀን 2015 ዓ.ም የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 እና የፓርቲዎቹ መተዳደሪያ ደንቦች በሚያዙት መሰረት ጠቅላላ ጉባኤዎቻቸውን እንዳያደርጉ በመንግስት መከልከላቸው ጉዳዩ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያሳዩ ድርጊቶች ናቸው፡፡

## ተያያዥ የህግ ድንጋጌዎች፡

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (UDHR) አንቀጽ 3፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል-ኪዳንም (ICCPR) በአንቀጽ 6(1) እና 9(1) ላይ እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት እንዳለው ያረጋግጣል። ይህንኑ መብት በማረጋገጥ፣ መንግሥታት በቃል-ኪዳኑ

(ICCPR) የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸውም በአንቀጽ 2(1) እና 2(2) ይደነግጋል። የአፍሪካ ቻርተር በሰዎች እና ህዝቦች መብቶች (ACHPR) አንቀጽ 4 ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደህንነት መብቱ ሊከበርለትና ሊጠበቅለት እንደሚገባና እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ ሊነፈግ እንደማይችል ተመላክቷል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 14 “ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው” ሲል ይደነግጋል። በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 15 ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት እንዳለውና በሕግ ከተደነገገው ውጪ ሕይወቱን ሊያጣ እንደማይችል በግልፅ ደንግጓል፡፡ በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት በአንቀጽ 16 ላይ ማነም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው ሲል ያስቀምጣል፡፡ በእነዚህ ዓለም አቀፍ፣ አህጉር አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ህጎች ላይ የመንግስት ዋነኛ ኃላፊነት የዜጎችን መብት የማክበር፣ የማስከበር እና የሟሟላት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን የመንግስት የጸጥታ አካላት ስልጣናቸውን አላግባብ በመጠቀም ከዳኝነት ውጪ የሆነ ግድያ ሲፈጽሙ ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የሚያሳይ እና በወንጀል ተጠያቂ ሊያስደርግ የሚገባው ነው፡፡

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (UDHR) አንቀጽ 13፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል-ኪዳንም (ICCPR) አንቀጽ 12 ላይ በአንድ አገር ግዛት ውስጥ በሕጋዊ መንገድ ያለ ማንኛውም ሰው በዚያ አገር ውስጥ በነጻነት የመንቀሳቀስ መብት እንዳለው ይደነግጋሉ፡፡ የአፍሪካ ቻርተር በሰዎች እና ህዝቦች መብቶች (ACHPR) አንቀጽ 6 ላይ ማንኛውም ሰው ነጻነቱና አካላዊ ደህንነቱ ተጠብቆለት የመኖር መብት አለው ሲል ይደነግጋል፡በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት በአንቀጽ 17 እና 32 ላይ ማንኛውም ሰው የአካል ነጻነት መብት እንዳለው እና በነጻነት በፈለገው አካባቢ የመዘዋወር መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ አባል ሀገር ባትሆንም ሰዎችን አስገድዶ ከመሰወር ለመጠበቅ የወጣው ዓለም አቀፍ ስምምነት(International Convention for the Protection of All Persons from Enforced Disappearance) በአንቀጽ 1(1) ላይ ማንም ሰው ለአስገድዶ መሰወር ተጋላጭ መሆን እንደሌለበት በመደንገግ ይህንን ወንጀል የፈጸሙ አካላትን መንግስት በወንጀል ተጠያቂ እንዲያደርጋቸው ይደነግጋል፡፡

የኢትዮጵያ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ ምዕራፍ 3 ላይ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ሰዎች ጋር በተያያዘ ያለውን የስነስርዓት ህግ ሲዘረዝር አንቀጽ 172 ላይ በቅርብ ወደሚገኝ ፍርድ ቤት ወድያውኑ መቅረብ እንዳለባቸው፣ ፍርድ ቤት የቀረበው ጉዳይ የጊዜ ቀጠሮ ወይም ወደ ላይ ፍርድ ቤት መቅረብ የሚያስፈልገው ከሆነ ለአካለ መጠን ያልደረሰውን ወጣት ነገሩ በሚሰማበት ቀን ለማቅረብ ለሚችሉ ለወጆቹ፣ ለሞግዚቱ ወይም ለዘመዶቹ፤ እነሱም የሌሉ እንደሆነ ለማረሚያ ቤት ሳይሆን ለአንድ ድርጅት ወይም ራሱን ለቻለ ጨዋ ሰው እንደሚሰጥ ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም ይህ ሳይሆን ቀርቶ ታዳጊውን በጊዘ ቀጠሮ ምክንያት በመረሚያ ቤት ማቆየት የህግ ስነስርዓትን ያላከበረና የታዳጊውን ሰብዓዊ መብት የሚገፍ ድርጊት ይሆናል ማለት ነው፡፡

## የኢሰመጉ ጥሪ፡

- የአማራ ክልል መንግስት በምስራቅ ጎጃም  ዞን ደብረ ኤልያስ ወረዳ በብሔረ ብፁዓን አጼ መልካ ስላሴ ገዳም ላይ ጥቃት በመፈጸም የሰው ህይወት ያጠፉ እና አካል ላይ ጉዳት ያደረሱ የመንግስት የጸጥታ አካላትን ተገቢውን ማጣራት በማድረግ በህግ እንዲጠይቅ እንዲሁም የኢሰመጉ የምርመራ ባለሙያዎች ወደቦታው ሄደው የምርመራ ስራ እንዳያደርጉ የሚጣሉ ገደቦችን እንዲያስቆም፣
- በሲዳማ ክልል እና በኦሮሚያ ክልል አዋሳኝ አካባቢዎች ላይ የተቀሰቀሰውን ብሔርን መሰረት ያደረገ ግጭት የሁለቱም ክልል መንግስታት ከደረሰው ጉዳት በላይ ሳይደርስና ችግሩ ሳይስፋፋ በሰላማዊ መንገድ ዘላቂ መፍትሔ እንዲያበጁ፣
- በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ወለጋ ዞን ሳሲጋ ወረዳ ከህግ አግባብ ውጪ ሶስት ሰዎችን የገደሉ የመንግስት የጸጥታ አካላትን የክልሉ መንግስት ተገቢውን ምርመራ በማድረግ በህግ ተጠያቂ እንዲያደርግና በተጨማሪም በጉጂ፣ ቦረናና ባሌ አካባቢዎች ከአስተዳደር ወሰን ጋር በተያያዘ በጉጂ ዞን በተለያዩ አካባቢዎች በተደረጉ ሰልፎች ላይ በሰልፍ ላይ የነበሩ ሰዎችን የገደሉ የጸጥታ አካላትን የክልሉ መንግስት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ በህግ እንዲጠይቅ፣
- የኦሮሚያ ክልል መንግስት በአጠቃላይ በክልሉ ባሉ በምዕራብ ሸዋ ዳኖ ወረዳ ውስጥ በሚኖሩ ሰላማዊ ሰ ዎች ላይ በታጣቂ ቡድኖች እና በመንግስጥ የጸጥታ አካላት የሚፈጸሙ ግድያ፣ የአካል ጉዳት፣ እስራት፣ ድብደባ፣ ንብረት ውድመትና ማፈናቀሎችን እንዲያስቆምና ይህንን ድርጊት የሚፈጽሙ ሰዎች በህግ ተጠያቂ እንዲያደርግ እንዲሁም መሰል ጥቃቶች በምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋና ቄለም ወለጋ ዞኖች በተደጋጋሚ የሚፈጸሙ በመሆኑ ለእነዚህ አካባቢዎች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የህዝቡን ደህንነት እንዲያረጋግጥ፣
- በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ሀላባ ዞን ሀላባ ቁሊቶ ከተማ ተማሪ ሊዲያ አበራ ላይ የተፈጸመው ድርጊት ተገቢውን የህግ ስነ-ስርዓት ያልተከተለ በመሆኑ የሀላባ ቁሊቶ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተገቢውን ማስተካከያ እንዲያደርግና በአካባቢው ላይ በተማሪዎች ላይ በሐይማኖት / እምነት ምክንያት የሚደርስን ድብደባ፣ ዛቻ እና ማስፈራራት እንዲያስቆም፣
- በጋጮ ባባ ወረዳ ኩይሌ ቀበሌ ለወረዳ አስተዳደር አቤቱታ ለምን አቀረባችሁና ለኢሰመጉ መረጃ ለምን ትሰጣላችሁ በሚል ከህግ አግባብ ውጪ በእስር ላይ የሚገኙ አራት ሰዎችን   የ ጋጮ ባባ ወረዳ በአስቸኳይ ከእስር እነዲለቅ፣
- በጋጮ ባባ ወረዳ በህዝብ የተመረጠን የቀበሌ አስተዳደር ከህግ አግባብ ውጪ ከሀላፊነት ያነሱና በእስር እንዲቆይ ያደረጉ አካላትን የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግስት ተገቢውነ ማጣራት በማድረግ በህግ ተጠያቂ እንዲያደርግ፣
- በአማሮ ልዩ ወረዳ ያሉ ተፈናቃዮች ላይ ማንነትን መሰረት ያደረገ አድሎ የሚፈጽሙ አካላትን  ልዩ ወረዳው እንዲሁም የደቡበ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መ ንግስት በአስቸኳይ እንዲያስቆም እንዲሁም በልዩ ወረዳው ላሉ ተፈናቃዮች ያለምንም አድሎ ድጋፍ እንዲደረግ እና በማንነታቸው ምክንያት ንብረታቸው ለተወረሰባቸው ሰዎች ንብረታቸው እንዲመለስ፣
- በደራሼ ልዩ ወረዳ በካቢኔው ውስኔ መሰረት ለተጎጂዎች እርዳታ የሰጡ ስምንት ሰዎችን ያሰሩ የአካባቢው አመ ራሮችን የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግስት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ በህግ እንዲጠይቅና የታሰረትን ሰዎች የአካል ነጻነት መብት እንዲያስከብር እንዲሁም በአካባቢው

ጋጮ ባባ ወረዳ እና አማሮ ልዩ ወረዳን ጨምሮ ስልጣንን ያለአግባብ በመጠቀም የሚሰሩ ወንጀሎችንና ይህንን ተከትሎ የሚደርሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግስት ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ሁኔታዎችን እንዲያሻሽል፣

- በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ አስተዳደር ውስጥ እየተካሄደ ካለው የቤት ፈረሳ እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ለሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የሚመለከተው የመንግስት አካል ለጉዳዩ አስፈላጊውን በቂ ትኩረት እንዲሰጥ፣
- በየኛ ቲቪ ጋዜጠኛ በሆነው ንጉሴ ብርሀኑ እና በመምህርና የማህበረሰብ አንቂ በሆነው ታዬ ቦጋለ አረጋ ላይ እገታ የፈጸሙ አካላትን በማጣራት መንግስት በህግ ተጠያቂ እንዲደርግና መሰል ድርጊቶች መደጋገማቸውና ጥቃት አድራሾችም ላይ የህግ ተጠያቂነት አለመመስረቱ ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩረት አለመሰጠቱን የሚያሳይ በመሆኑ መንግስት ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጥ፣
- በሚዲያ ተቋማት ላይ የሚደረጉ ዝርፊያዎች እንዲሁም በሰብዓዊ መብት ተቋማት ላይ የሚደረጉ ዝርፊያዎች የሲቪል ምህዳሩን እና የሚዲያውን ተሳትፎ አደጋ ውስጥ የሚከ ቱ በመሆ ናቸው መንግስት ይህንን ድርጊት በአስቸኳይ እንዲያስቆም፣
- የፖለቲካ ፓርቲዎች ጠቅላላ ጉባኤዎቻቸውን ህጉ በ ሚያዘው መሰረት እንዳያደርጉ የሚደረጉ ክልከላዎች የፖለቲካ ምህዳሩ ላይ አደጋን የሚጥ ሉ ድርጊ ቶች እና ፖለቲካ ፓርቲዎችን በማዳከም ሰዎች በአገራቸው መንግስት ውስጥ በቀጥታ ወይም በነጻ በመረጧቸው ወኪሎቻቸው አማካኝነት የመሳተፍ መብታቸው ላይ ተጽእኖን የሚፈጥ ሩ ድርጊ ቶች በመሆ ናቸው መንግስት እነዚህን የሚያደርጉ አካላት በህግ እንዲጠይቅና ከመሰል ድርጊት እንዲቆጠብ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ